1. <u>የኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድአሰጣጥ</u>

የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰጠው የሚያመለክት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ፡-

1.1 መታወቂያውን ለማግኘት ዜግነት ከወሰደበት አገር የተሰጠውና አገልግሎቱ ቢያንስ ለስድስት ወራት የፀና ፓስፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

1.2 ከላይ በተራ ቁጥር 1.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሚከተሉት አንዱን ሙሉ ስም ከነአያት የሚገልጽና ዋናውን ከሁለት ቅጂዎች ጋር የሰነድ ማስረጃ በተጨማሪ ማቅረብ አለበት፡፡

1.2.1 የአመልካቹ አግባብ ካለው አካል የተሰጠና የተረጋገጠ የልደት ምስክር ወረቀት ማስረጃ ቅጂ፤ ወይም

1.2.2 የአመልካቹ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፓስፖርት ዋናውን ወይም ቅጂ፤ ወይም

1.2.3 ሥልጣን ባለው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ/ከነበሩ የስጋ /Biological/ ወላጆች የተገኘ የወራሽነት ማስረጃ ወይም

1.2.4 ሥልጣን ካለው ፍ/ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ በኢትዮጵያውያን ወላጆቹ በጉዲፈቻነት የተሰጠ የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ቅጅ፣

1.2.5 ሥልጣን ካለው ፍ/ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የኢትዮጵያ ተወላጅነት የሰው ወይም የሰነድ ምስክርነት ማስረጃ ቅጅ፣

1.2.6 ሥልጣን ካለው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት የተሰጠና አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ አባቱ ወይም እናቱ ወይም አያቱ ወይም ቅድመ አያቱ ቢያንስ በአንዱ የኢትዮጵያን ዜግነት ይዞ የነበረ መሆኑን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ፣

1.3 ከላይ በተራ ቁጥር 1.1 እንዲሁም ከተራ ቁጥር 1.2.1 እስከ 1.2.6 ከተመለከቱት አንዱን በተጨማሪ

1.3.1 መታወቂያውን ለማግኘት የሚያስፈልገውን የጣት አሻራ በሚሲዮን ጽ/ቤት ወይም በአካባቢው በሚገኝ የፖሊስ ጽ/ቤት አሻራ የሰጠበት ሰነድ ሲቀርብ /የኢትዮጵያ ፓስፖርት ጥያቄ በሚስተናገድበት ሁኔታ/ ወይም በአገር ውስጥ በኢሚግሬሽን ጽ/ቤት መሰጠት አለበት፤

1.3.2 ሦስት በቅርብ ጊዜ የተነሳ ሙሉ ፊት የሚያሳይ ለፓስፖርት በሚሰጠው ልክ /3x4 ሳ.ሜ/ የሆነ ፎቶግራፍ እና

1.3.3 ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በሁለት ቅጅ መሙላት፤ የአመልካች ትክክለኛ አድራሻ(ስልክ፣ ኢሜል እና የፓስታ አድራሻ) በትክክል መሞላት አለበት

በአገር ውስጥ ሲሆን በኢሚግሬሽን ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሆን በሚኖሩበት አገር ለሚገኘው /ለተወከለው/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮን በማቅረብ ለአምስት ዓመት የሚያገለግል የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ይሰጣል፡፡

2. <u>አካለመጠንላልደረሱየኢትዮጵያተወላጅልጆችስለሚሰጥአገልግሎት</u>

2.1 እድሜው 18 ዓመት ያልሞላው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የተቀበለ የውጭ ዜግነት ያለው ሰው ልጅ የግሉ መታወቂያ ማውጣት ሳይገደድ በወላጅ አማካኝነት የሚከተሉት ከሁለት ቅጅዎች ጋር ሲሟሉ

2.1.1 የልጁ/የልጇን ሕጋዊ የልደት የምስክር ወረቀት፤

2.1.2 ቢያንስ ለስድስት ወራት አገልግሎቱ የጸና የልጁ/የልጇን ፓስፖርት፤

2.1.3 የወላጅ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እና

2.1.4 ልጁ/ልጅቷ በቅርብ ጊዜ የተነሳው/ችው ሙሉ ፊትን የሚያሳይ ሦስት ጉርድ ፎቶግራፍ ከሁለት ማመልከቻ ቅጽ፣

2.2 እድሜው 14 ዓመትና በላይ የሆነና 18 ዓመት ያልሞላው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የተቀበለ የውጭ አገር ሰው ልጅ የጣት አሻራውን በአገር ውስጥ ሲሆን በኢሚግሬሽን ከኢትዮጵያ ውጭ ሲሆን በሚኖርበት አገር ለተወከለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮን ሲያቀርብና የመታወቂያ አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ለአምስት ዓመት የሚያገለግል መታወቂያ የልጁ እድሜ 18 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ብቻ ይሰጣል፡፡

2.3 የኢትዮጵያ ተወላጅ ልጅ እድሜው ለአካለ መጠን ሲደርስ በራሱ ጠያቂነት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ አሰጣጥ መስፈርትን ሲያማላ የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡

2.4 ከላይ በተራ ቁጥር 2.2 የተመለከተው ቢኖርም በወላጅ ወይም በአሳዳጊ አመልካችነት በተራ ቁጥር 1.1 እንዲሁም በተራ ቁጥር 1.2 ሥር ከተዘረዘሩት መካከል አንዱን አሟልቶ እድሜው ከ14 ዓመት በላይና 18 ዓመት ያልሞላው አሻራ ሰጥቶ ከተራ ቁጥር 2.1.1 እስከ 2.1.4 የተዘረዘሩት መሟላታቸው ሲረጋገጥ ለአምስት ዓመት የሚያገለግል መታወቂያ ካርድ እንዲያገኝ ይፈቀድለታል፡፡

3. <u>የኢትዮጵያተወላጅየትዳርጓደኛስለሚሰጥየኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድ</u>

3.1 ለኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ያለው/ያላት የውጭ አገር ዜጋ ለትዳር ገ<ደኛው/ገ<ደኛዋ/ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እንዲሰጥለት/እንዲሰጥላት ከፈለገ/ች

3.1.1 ቢያንስ ሁለት /2/ ዓመት የሆነው የተረጋገጠ የጋብቻ ማስረጃ፤

3.1.2 የመታወቂያ ጠያቂው አገልግሎቱ ቢያንስ ለስድስት ወራት የጸና ፓስፖርት፣

3.1.3 የባል/የሚስት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ኮፒ፤

3.1.4 የትዳር ጓደኛው/ዋ በቅርብ ጊዜ የተነሳው/የተነሳችውን/ ሦስት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍና

3.1.5 ትዳሩ የፀና ለመሆኑ ጥንዶቹ በጋራ የፈረሙት የቃለ መሃላ ሰነድ፣

3.1.6 ለዚህ ዓላማ የተዘጋጀው የማመልከቻ ቅጽ ተሞልቶ ከሁለት ቅጅ ጋር፣

3.1.7 የጣት አሻራ ሲሰጥ፣

ከአገር ውጭ ሲሆን ለኢትዮጵያ ሚሲዮን በአገር ውስጥ ሲሆን ለኢሚግሬሽን ይቀርባል፡፡

3.2 ከላይ የተጠቀሱት ሲሟሉ ለ5 ዓመት የሚያገለግል የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሚስት/ባል መሆኑን ወይም መሆንዋን የሚገልጽ የመታወቂያ ካርድ እንድታገኝ/እንዲያገኝ ይፈቀዳል፡፡

4. <u>የኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድጥያቄበሚሲዮኖችስለሚቀርብበትሁኔታ</u>

4.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ለማግኘት በውጭ አገር በሚገኙ የኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ጥያቄው ሲቀርብ አመልካች በአካል ቀርቦ ወይም በሚሲዮኑ በሚዘረጋው የአሰራር ስርዓት መሠረት ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ እና ተፈላጊ ማስረጃዎችን በተመዘገበ የፖስታ መልእክት በመላክ ጥያቄውን ያቀርባል፡፡ የፖስታ ወይም የመላላኪያ ክፍያዎች በአመልካቹ የሚሸፈኑ ይሆናሉ፡፡

4.2 ሚሲዮኑ በተራ ቁጥር 1 የተገለጹትን አስፈላጊ መረጃዎች በማሟላት ለኢሚግሬሽን ይላካል፡፡

4.3 የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ተገቢ ማስረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የተወላጅነት ማረጋገጫ ካርዱን አዘጋጅቶ ለሚሲዮኑ ይልካል፡፡ ሚሲዮኑም እንደ ሁኔታው አመቺነት ግለሰቡ በግንባር ሲቀርብ ወይም በፖስታ ቤት በመላክ ያስረክባል፡፡

4.4 አመልካች በአገር ቤት የሚገኝ ከሆነ ጥያቄውን በቀጥታ ለኢሚግሬሽን በአካል በማቅረብ መስፈርቶችን አሟልቶ እና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርዱን ማግኘት ይቻላል፡፡

5. <u>በአገርቤትለሚሰጥአገልግሎትየኢትዮጵያተወላጅነትየመታወቂያካርድመያዝስለማስፈለጉ</u>

5.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ ማንኛውም ትውልድ ኢትዮጵያዊ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባና ሲወጣ እንዲሁም ማንኛውም አገልግሎት ሲጠይቅ ያገኘበትን አገር የፀና ፓስፖርትና የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ማሳየት ይጠበቅበታል፡፡

5.2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ የውጭ ሃገር ዜጋ ወደ አገር ቤት ሲገባና ከኢትዮጵያ ሲወጣ በዜግነት ፓስፖርቱ ላይ የመግቢያና የመውጫ ቀን ማህተም ተመቶበት እንዲገባና እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

5.3 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት በውጪ ሃገር ለኢትዮጵያ ሚሲዮን በሃገር ውስጥ ለኢሚግሬሽን በማመልከት መታደስ ይኖርበታል፡፡ የአገልግሎት ጊዜው ባበቃ መታወቂያ አገልግሎት አይሰጥም፡፡

6. <u>የኢትዮጵያተወላጅመታወቂያካርድእድሳት</u>

6.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ እድሳት አገልግሎት የሚሰጠው ቀጥሎ የተመለከቱትን በሁለት ቅጅዎች በማሟላት ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሚሲዮን ወይም ለኢሚግሬሽን ሲቀርብ ነው፡፡

6.1.1 ዜግነት ካገኘበት አገር የተሰጠውና ቢያንስ ለስድስት ወራት አገልግሎቱ የጸና ፓስፖርት፣

6.1.2 ቀደም ሲል የተሰጠው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ዋናው ከሁለት ቅጅ ጋር፣

6.1.3 በቅርብ ጊዜ የተነሳ ሙሉ ፊቱን የሚያሳይ 3 ጉርድ ፎቶግራፍ፣

6.1.4 የጣት አሻራ በአገር ውስጥ በኢሚግሬሽን፣ በውጭ አገር በሚሲዮን ጽ/ቤት ወይም በአካባቢው በሚገኝ የፖሊስ ጽ/ቤት አሻራ የሰጠበት ሰነድ፣ ቀድሞ ከተሰጠ በድጋሚ አያስፈልግም፣

6.1.5 በጋብቻ መሠረት የተሰጠ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እድሳት ጥያቄ ትዳሩ የጸና ስለመሆኑ ጥንዶቹ በጋራ የፈረሙበት የቃለ-መሃላ ሰነድ ተያይዞ ሲቀርብና አገልግሎቱ የፀና የባል/የሚስት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ዋናው ከሁለት ቅጅ ጋር፣

6.1.6 የእድሳት ማመልከቻ ከሁለት ቅጅና ተገቢውን ክፍያ ሲፈጽም መታወቂያው ለ5 ዓመት ይታደሳል፡፡

6.1.7 የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ የአገልግሎት ጊዜው ከማብቃቱ ከስድስት ወር በፊት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፣

7. <u>የኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድስለሚሰረዝበትሁኔታ</u>

7.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ በአዋጅ ቁጥር 270/94 በአንቀጽ 14 መሠረት እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

7.2 መታወቂያው የተገኘው ሌላ ሰው መስሎ በመቅረብ ወይም ስለራሱ ትክክለኛውን ነገር በመደበቅ ወይም የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ከሆነ፣

7.3 የመታወቂያው ባለቤት በሽብርተኝነት ተግባር ወይም ሰዎችን ወይም የተከለከሉ እጾችን ወይም የጦር መሳሪያዎችን ወይም ገንዘብ በሕገ ወጥ መንገድ በማዘዋወር ጥፋተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ፣

7.4 የመታወቂያው ባለቤት በሌላ አገር መንግሥት በመደበኛ ውትድርና ወይም በደህንነት ሥራ ማገልገሉ ከተረጋገጠ፣

7.5 መታወቂያውን ይዞ መቆየቱ ለሕዝብና ለአገር ጥቅም እንዲሁም ለአገርና ለሕዝብ ፀጥታና ደህንነት ተገቢ አለመሆኑ በበቂ ማስረጃ ከተረጋገጠ፣

7.6 በኢሚግሬሽን አዋጅ ቁጥር 354/1995 መሠረት የአደገኛ እጽ ሱስ ተገዠ መሆኑ ከተረጋገጠ ወይም አደገኛ ወንጀለኛ መሆኑ ከታወቀ፣

7.7 የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ የትዳር ጓደኛ ጋብቻ በፍቺ ወይም በሞት ሲፈርስ በጋብቻው የተሰጠው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርዱን የያዘው ባለቤት በገባው ግዴታ መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካላሳወቀ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

8. <u>የኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድእርማት</u>

8.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ እርማት የሚደረገው የመታወቂያ ካርዱ ባለቤት የሚፈለገውን እርማት ጠቅሶ ሲያመለክትና እርማቱን ማድረግ ስለማስፈለጉ አሳማኝ ምክንያት በበቂ የሰነድ ማስረጃ ተደግፎ ሲቀርብ ነው፡፡

8.2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ እንዲታረም ጥያቄ የቀረበው በመጀመሪያ መታወቂያ ከሰጠው አካል ውጭ ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ ጥያቄው የቀረበለት የኢትዮጵያ ሚሲዮን ወይም ኢሚግሬሽን ምትክ የተወላጅ መታወቂያ ካርድ ከመስጠቱ በፊት መጀመሪያ የሰጠውን አካል በእርማቱ ጥያቄ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

8.3 እርማቱ የስም ለውጥ ከሆነ ሥልጣን ከተሰጠው ፍርድ ቤት የተሰጠ እና አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ማስረጃ፣ በጋብቻ ምክንያት የስም ለውጥ ከሆነ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የጋብቻ ማስረጃ እና ትዳሩ የፀና ለመሆኑ ጥንዶቹ በጋራ የፈረሙበት የቃለ መሃላ ሰነድ ሁለት ቅጅ እንዲሁም የስም ለውጡ በጉዲፈቻነት ከሆነ አግባብ ባለው አካል የተረጋገጠ ሕጋዊ የሰነድ ማስረጃ ከሁለት ቅጅ ጋር ማቅረብ አለበት፡፡

8.4 መታወቂያ ካርዱን መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች አስመልክቶ የሚደረግ እርማት ከሁለት ጊዜ በላይ ከሆነ በሚሲዮኑ መሪ ወይም በኢሚግሬሽን ዳይሬክተር የሚወሰን ይሆናል፡፡

9. <u>የጠፋወይምየተበላሸየኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድስለመተካት</u>

9.1 አመልካች ባለው የክፍያ ደንብ ለጠፋ ወይም ለተበላሸ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የሚጠይቀውን ክፍያ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

9.2 ለጠፋ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርዱ ምትክ ሊሰጠው የሚችለው መታወቂያ ስለመጥፋቱ ከአካባቢው ፖሊስ ወይም አግባብ ካለው አካል በቂ የሆነ ማስረጃ ሲቀርብና የጠፋው የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ዝርዝር መረጃ ለኢሚግሬሽን ወይም ለሚሲዮኑ ሲቀርብ ነው፡፡

9.3 የጠፋው ወይም የተበላሸው መታወቂያ በጋብቻ ምክንያት የተሰጠ ከሆነ የኢትዮጵያ ተወላጅ የውጭ አገር ዜጋ የትዳር ጓደኛ ትዳሩ የፀና ለመሆኑ ጥንዶቹ የፈረሙበት የቃለመሃላ ሰነድ በሁለት ቅጅ መቅረብ አለበት፡፡

10. <u>የኢትዮጵያተወላጅነትመታወቂያካርድስለመመለስ</u>

10.1 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ ሰው በአዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀጽ 13 መሠረት በማናቸውም ጊዜና ምክንያት በጽሁፍ ማመልከቻ በማቅረብ መታወቂያ ካርዱን መመለስ ይችላል፡፡

10.2 የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርዱን ለመመለስ ማመልከቻ ያቀረበ የኢትዮጵያ ተወላጅ በሱ ምክንያት የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ የተሰጣቸው የቤተሰብ አባላትን መታወቂያ ካርድ መመለሱ ከተረጋገጠ በኋላ ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

11. <u>የኢትዮጵያተወላጅሙብቶችቀሪስለሚሆኑበትሁኔታናግዴታዎች</u>

11.1 በቁጥር 10 መሠረት የመታወቂያ ካርዱን የመለሰ የኢትዮጵያ ተወላጅ ወይም የኢትዮጵያ ተወላጅ ባል/ሚስት በአዋጅ ቁጥር 270/94 አንቀጽ 5፣ 8/4/ እና 8/6/ መሠረት ያገኛቸው ማንኛቸውም መብቶች ቀሪ ይሆናሉ፣

11.2 የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ የያዘ ሰው በአዋጁ የተሰጡት መብቶች በሙሉ ቀሪ ሆነው እንደማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ተቆጥሮ በአገሪቱ ሕግ መሠረት ይስተናገዳል፡፡ መታወቂያው ለስድስት ወራት ሳይታደስ ከቆየ መታወቂያ ካርዱን እንደመለሰ ተቆጥሮ በአዋጁ ያገኛቸው መብቶች በሙሉ ቀሪ ይሆናሉ፡፡

11.3 የመታወቂያ ካርዱን የመለሰ ሰው መታወቂያውን በተጠቀመበት ጊዜ የገባቸውን ውሎች ወይም ሌሎች ግዴታዎችን የማክበርና የመፈጸም ሃላፊነት አለበት፡፡

<u>ማስታወሻ</u>

አሳማኝ ምክንያት ሲኖር የአስቸኳይ አገልግሎት የተዘጋጀ ሲሆን አመልካቾች ለፈጣን መልዕክት የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ ወጪ በራሳቸው በመሸፈን ሰነዶቻቸውን ከኤምባሲው ለኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ እንዲተላፍ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለአስቸኳይ አገልግሎቱ ከመደበኛው ክፍያ ላይ 30%(ሰላሳ ፐርሰንት) ተጨማሪ ክፍያ የሚጠየቅ ሲሆን፣ አገልግሎቱም በአማካኝ በ15 ቀናት ውስጥ ይሰጣል፡፡

አመልካቾች ተዘጋጅቶ የመጣላቸውን የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ እጅግ ቢዘገይ በሶስት ወራት ውስጥ ተከታትለው መረከብ አለባቸው፡፡ ተዘጋጅተው መጥተው በሶስት ወራት ውስጥ ተረካቢ ያላገኙ የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርዶች ለኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ተመላሽ ይደረጋሉ፡፡

ክፍያውን አስቀድመው ይፈጽሙ /የክፍያውን ዝርዝር ከታች ይመልከቱ/

ክፍያ የተፈጸመበትን ደረሰኝ እና ከተሰራ በኋላ ተመልሶ የሚላክበት አድራሻ የተጻፈበት ባዶ ፖስታ ከማመልከቻው ጋር አያይዘው ይላኩ፤ የፖስታ ክፍያውን ይዘትና ክፍያ ከታች ይመልከቱ፤

<u>የፎቶይዘት</u>:- አመልካቹ የሚያቀርበው ፎቶግራፍ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡፡

ባለ ቀለም (coloured not black and white) መጠኑ 3x4 cm የሆነ 3 ፎቶ፣

የአመልካቹ ፊት መጠን በፎቶው ላይ 3/4ኛውን የሚሸፍን፣

ፊት ለፊት የተነሳና በተቻለ መጠን ሁለቱ ጆሮዎች የሚያሳይ፣

ነጣ ያለ የፎቶግራፍ ጀርባ /BACKGROUND/ ያለው፣

ያለመነጽር የተነሳ ቢሆን ይመረጣል፣

ከእምነት ጋር የተያያዘ እስካልሆነ ድረስ ኮፍያ ወይም የራስ መሸፈኛ የሌለበት፣

# Identification Cards of Persons of Ethiopian Origin

| Type of Documents | Duration of service | SEK |
|---|---|---|
| Adults | 5 years | 1,740.00 |
| Children Below 18 years of Age | | 174.00 |
| Replacement of an Expired Identification Card | | 1740.00 |
| Replacement of a Lost Identification Card for the first time | | 2,088.00 |
| Replacement of a lost Identification Card for the Second time | | 2,610.00 |
| Replacement of a Lost Identification Card for the Third or more time | | 3,480.0 |

የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ የአገልግሎት ጊዜው ከማብቃቱ ከስድስት ወር በፊት ጥያቄው መቅረብ ይኖርበታል፣

ለፖስታ መላኪያ ምንም አይነት ክፍያ መከፈል የሌለበት ሲሆን ከዚህ በታች በተጠቀሰው መሰረት የፖስታ መላኪያ መላክ ይኖርበታል፡፡

ክፍያው በሌላ ሰው የተፈፀመ ከሆነ ክፍያ የተፈፀመለት ሰው ስም በትክክል በሚላከው የክፍያ ደረሰኝ ላይ በእጅ መፃፍ ይኖርበታል፡፡

ኤምባሲው ለአገልግሎቱ ከሚጠይቀው የክፍያ መጠን ውጭ የሚፈፀም ማንኛውም በትርፍ ክፍያ አይመለስም፡፡

ክፍያን በፖስታ መላክ አይቻልም፡፡

ክፍያመፈፀሚያ

Bank Giro no. 521-8235 write message instead of OCR No. OR

SEB Bank IBAN No. SE575000 0000 0527 7110 6248, Bic-Code ESSESESS

የመላኪያፖስታይዘት

- ከስዊድን

  በስዊድን ነዋሪ የሆኑ የተዘጋጀላቸውን የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ የመመለሻ የተቀባይ አድራሻ በትክክልና በግልፅ የተፃፈበትና ባለ 104 ክሮነር ስታምፕ/ቴምብር የተለጠፈበት ባዶ ፖስታ አብሮ መላክ ይኖርበታል፡፡ የመላኪያ ክፍያ ተቀባይነት የለውም፡፡

- ከስዊድንውጭካሉሀገሮች

  ከስዊድን ውጭ ካሉ ሀገሮች በፖስታ ለሚቀርቡ ማመልከቻዎች የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርዱ ከተሰራ በኋላ መልሶ ለመላኪያ የሚሆን የተቀባይ አድራሻ በግልፅ የተፃፈበት ባዶ ከ12 ኢንተርናሽናል ኩፖን (ለ1 ካርድ ከአንድ ፓስፖርት ጋር፣ 14 ኩፖን ከሁለት ፓስፖርቶች ጋር፣) አብሮ መላክ ይኖርበታል፡፡

  ለፖስታ መላኪያ ምንም አይነት ክፍያ ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች ክፍያ የተፈፀመበት ኢንቨሎፕ/ፖስታ አያይዘው መላክ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከላይ በየዘርፉ የተጠቀሱትን መስፈርቶችና ዶክመንቶች ሳያሟላ የሚቀርብ ማንኛውም የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ማመልከቻ ለአመልካቹ ተመላሽ ይደረጋል፡፡